

## የተሻሻለ የወተት ከብቶች

# አያያዝ መመርያ

## የወተት ላሞች ቤት አሰራር፣አዛባ አያያዝና አጠቃቀም

2010 ዓ.ም

SNV

Designed & Printed by
master print
አራት ኪሎ ፡፡ +251 111 557 788 ገርጂ ፡፡ +251 116 298 777
31362 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
www.masterprintaddis.com

## 3.1 የወተት ላሞች በረት አሰራርና አዛባ አያያዝና አጠቃቀም

**የወተት ላሞችን ምርትና ምርታማነት ከሚወስኑ ዋና ዋና ግብዓቶች ውስጥ የመኖና መጠጥ ውሀ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። የላሞች የመኖና የመጠጥ ውሀ ፍጆታ በዕድሜያቸው፣ ክብደታቸው እና ላሞች ያሉበት ሁኔታ (እንደ እርግዝናና የአለባ ሁኔታ) ይወሰናል።**

- በኢትዮጵያ በርካታ የአገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች ከወተት ከብቶች እርባታ ጋር ተያይዞ ጥሩ የበረት አሰራር ጥቅም ያለመረዳት ችግር አለ።
- ጥሩ የወተት ከብቶች በረት አሰራር የከብቶችን ምቾት በመጨመር የወተት ምርትን ያሻሽለል።
- በዚህ ክፍል ወጪ ቆጣቢ፣ ቦታ የማይፈጅ፣ የላሞችን ምቾት የሚጠብቅና በበረት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን የማያስተጓጉል በረት አሰራር ዘዴ በስዕላዊ መግለጫ በማስደገፍ ይቀርባል።
- የበረት ንፅህና አያያዝ የሚያስገኘው ጥቅምና ከከብቶች የሚገኘውን ሽንትና እበት /አዛባ/ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረጊያ ዘዴዎች ይገለፃሉ።



**ላሞችን በአግባቡ በተሰራ በረት ወስጥ ማኖር የሚያስገኘው ጥቅም**

- የወተት ከብቶችን በሚመች በረት ውስጥ ማስቀመጥ ከአላስፈላጊ ፀሐይ፣ ዝናብ እና ሙቀት በመከላከል የወተት ምርት ከፍ እንዲል፣
- በጣም በአነስተኛ ቦታ በርካታ የወተት ከብቶችን ለማርባት፣
- በበረት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን /እንደ አለባ፣ መኖ ማቅረብ፣ ፅዳት፣ ሕክምናና ማዳቀል/ ያለ እንከን/ችግር እንዲከናወን ለማድረግና ንፁህ ወተት ለማምረት፣
- ከብቶችን ከበሽታ ለመከላከልና ንፁህ ወተት ለማምረት፣
- ከብቶችን እንደየዕድሜያቸውና ምርታማነታቸው በተለየ ሁኔታ በመንከባከብ የሚያስፈልጋቸውን ልዩ እንክብካቤ ለማድረግ ያግዛል።

## ቁልፍ መልዕክት

- የወተት ከብቶችን በሚመች በረት ውስጥ ማስቀመጥ ከአላስፈላጊ ፀሐይ፣ ዝናብ እና ሙቀት በመከላከል የወተት ምርት ከፍ እንዲል፣
- በጣም በአነስተኛ ቦታ በርካታ የወተት ከብቶችን ለማርባት፣
- በበረት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን /እንደ አለባ፣ መኖ ማቅረብ፣ ፅዳት፣ ሕክምናና ማዳቀል/ ያለ እንከን/ችግር እንዲከናወን ለማድረግና ንፁህ ወተት ለማምረት፣
- ከብቶችን ከበሽታ ለመከላከልና ንፁህ ወተት ለማምረት፣
- ከብቶችን እንደየዕድሜያቸውና ምርታማነታቸው በተለየ ሁኔታ በመንከባከብ የሚያስፈልጋቸውን ልዩ እንክብካቤ ለማድረግ ያግዛል።

## 3.2 ጥሩ የበረት አሰራር ጥቅም

**ጥሩ የወተት ከብቶች በረት በአግባቡና በመጠኑ የተዘጋጁ የመኖና የውሀ ገንዳዎች፣ በቂ የማረፊያ ቦታ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦይ ያለውና ግድግዳውና ጣሪያው በአግባቡ አየር ማስተላለፍ የሚያስችል መሆን አለበት።**



ሞቃታማ ለሆኑ አካባቢዎች በጥሩ ሁኔታ የተገነባ በረት



በጥሩ ሁኔታ ባልተሰራ በረት የከብቶችን ንጽህና መጠበቅ ያስቸግራል

# ቁልፍ መልዕክት


- የሚሰራው በረት የአካባቢውን ሥነ-ምህዳር ከግምት ያስገባ መሆን አለበት። በሞቃት አካባቢዎች ለወተት ላሞች በረት ግድግዳ ማዘጋጀት አስፈላጊ አይደለም።
- የቤቱ ወለል ከብቶችን የማያዳልጥ፣ ላሞች ሲተኙ የማይጎረብጥ ፈሳሽ የማይቋጥር መሆን አለበት።
- የበረቱ አሠራር በበረቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን /ማለትም አለባ፣ መመገብ፣ ሕክምናና ማዳቀልን/ የማያስተጓጉል መሆን አለበት።
- የበረቱ የግንባታ ቁሳቁሶች ከአካባቢው በቀላሉ የሚገኙና ከፍ ያለ ወጪ የማይጠይቁ መሆን አለባቸው።

## 3.2 ...የወተት ከብቶች በረት ዲዛይንና የግንባታ ቁሳቁሶች

**በዘመናዊ የወተት ከብት እርባታ ውስጥ እንደ ጥገቱ ዕድሜና ሁኔታ በረት ማዘጋጀት የሚመከር ነው።**

- የጥጆች ጎጆ
- ያደጉ ጥጆች በጋራ የሚኖሩበት በረት
- የወተት ላሞች በረት
- የጊደሮች በረት
- የማለቢያ ቦታ
- የማዋለጃ ቦታ እና
- የታመሙ መለያ ቦታ የሚጠቀሱ ናቸው።

ነገር ግን የጥገቱ ቁጥር አነስተኛ ከሆነ ከላይ የተጠቀሱት የበረት ዓይነቶች ሁሉም በአንድ አካል በማከፋፈል ሊገነባ ይችላል።



የከብቶች መመገቢያ አሰራር

## 3.3 የከብቶች አዛባ አያያዝና አጠቃቀም

- የከብቶች አዛባ በውስጡ ከፍተኛ ኃይልና ንጥረ ነገሮች የያዘ በመሆኑ እንደቆሻሻ መቆጠር የለበትም፡፡ የወተት ላሞች አዛባ በአግባቡ ከተያዘ ከፍተኛ ሀብት ሲሆን በአግባቡ ካልተያዘ ደግሞ ቆሻሻ ይሆናል፡፡
- የከብቶች አዛባ በአግባቡ ለመጠቀም የበረት ግንባታው ዲዛይን ወሳኝ ሲሆን በየዕለቱ በአግባቡ እንዲፀዳ በማድረግ በአንድ አካባቢ በማጠራቀም ወደ ጥቅም መቀየር ይቻላል፡፡
- በዚህ አዛባ የአማራጭ ኃይል /ባዮ ጋዝና ባዮ ፊውል/ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ አላስፈላጊ የኤሌክትሪክ ወጪን ለመቀነስ ይቻላል፡፡ የባዮጋስ ተረፈ-ምርት/ባዮስለሪው ለኮምፖስት ዝግጅት ጠቃሚ ግብዓት ነው፡፡ በከብቶች አዛባ የተዘጋጀ ኮምፖስት ለሰብሎች ሁለንተናዊ እድገት የሚያስፈልጋቸውን ማዕድናት በማቅረብ የአፈርን ባህርያት በማሻሻል፣ በአፈር ውስጥ የአየር ዝውውርን በማሻሻልና ለተክሎች ስሮች እንዲመቻቸው በማድረግ ለምርት እድገት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
- ሶስት ዋና ዋና የኮምፖስት አሰራር ዘዴዎች ይታወቃሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ጉድጓድ በመቆፈር ኮምፖስት የማዘጋጀት ዘዴ ለአርሶ አደሮች ቀላልና ወጪ ቆጣቢ ነው፡፡




1. ለኮምፖስት ማዘጋጃነት በተመረጠ ጥላማና ውሀ ለማግኘት አመቺ በሆነ ቦታ ላይ ቢያንስ ሁለት ጉድጓዶች ማዘጋጀት፡፡
2. የባዮ ጋዝ ተረፈ ምርትን/ባዮስለሪ ወይም በውሀ የተበጠበጠ የከብቶች አዛባን ጨምሮ ለኮምፖስት ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ በስባሽ ግብአቶችን ማለትም የከብት ቀለብ ትራፊ፣ የቤት ጥራጊ፣ ደረቅና እርጥብ እፅዋት በጉድጓዶቹ አጠገብ ማቅረብ፡፡
3. በስዕሉ እንደሚታይው በስባሽ ግብአቶችን ተራ በተራ ከጉድጉዱ ውስጥ መጨመር፡፡ ይህ ሂደት ጉድጓዱ እስኪሞላ ድረስ ተደጋግሞ ይከናወናል፡፡የሚጨመረው ቁስ መጠን የስለሪውን እርጥበት ሊመጥን የሚችል መሆን አለበት፡፡
4. ከሁለት ወይም ሦስት ሳምንታት በኋላ የመጀመሪያው ጉድጓድ ሲሞላ ስለሪውን/የከብቶ አዛባውን ወደ ሁለተኛው ጉድጓድ በመጨመር እንደመጀመሪያው እንዲሞላ በማደርግ ያልተብላሉ አካላትን  በሚገባ እንዲብላሉ ማድረግ ይገባል፡፡